# ዜና አመዝኤ



## በዚህ ዕትም ውስጥ


ለመስከረም ወር ከ 156 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታና ከ3,900 በላይ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች ተመድቧል
ገጽ 2

ብሔራዊ ዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴ ዕርዳታ ለማሰባሰብ በተዘጋጀ ረቂቅ ዕቅድ ላይ ተወያየ
ገጽ 3

ወላጆቻቸውን በጎርፍ አደጋ ያጡ ህፃናት ወደ ማሳደጊያ ተቋም እንዲገቡ ተደረገ
ገጽ 4

የአመዝኤ የ1998 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም አጥጋቢ እንደነበር ተገለፀ፡፡
ገጽ 5




# በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ ወገኖች 27 ሺህ 175 ኩንታል ምግብና 498 ሺህ 231 ምግብነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ዕርዳታ ተልኳል

## ከ38 ሚሊዮን ብር በላይ በገንዘብና በዓይነት ተለግሷል

በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በተከሰተው የጎርፍ አደጋ የተጎዱ ወገኖቻችንን ለመርዳት የፌዴራል አመዝኤ 27 ሺህ 175.7 ኩንታል ምግብና 498 ሺህ 231 ምግብ ነክ ያልሆነ ቁሳቁስ ዕርዳታዎችን ወደየአካባቢዎች ላከ፡፡

ከዚሁ ኤጀንሲው ከላከውና ግምታቸው ብር 14 ሚሊዮን 316 ሺህ 348.7 የሆኑ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ዕርዳታ ውስጥ አደጋው ከተከሰተበት ሐምሌ ወር ወጨረሻ ጀምሮ እስከ መስከረም 22 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ 24 ሺህ 469 ኩንታል የምግብ እህል ፣ ፍርኖ ዱቄት ፣ ጥራጥሬና ዘይት ፣ 2 ሺህ 706.7 ኩንታል ብስኩት፣ ፋሚክስና አጥሚት ፣ 505 ካርቶን



ወተትና የታሸገ ምግብ ፣ 10 ጣሳ የወተት ዱቄት፣ በቁጥር 15 ሺህ 890 ልዩ ልዩ አልባሳት ፣ በቁጥር 395 የተለያየ መጠን ያላቸው ድንኳኖች ፣ በቁጥር 4 ሺህ 767 ጀሪካኖች ፣ 71 ሺህ 37 ጭልፋ ፣ ማንኪያ ፣ የሻይ ማንቆርቆሪያ ፣ ብረት ድስት ፣ ኩባያና ሳህን፣ 1 ሺህ 150 ፍራሽ ፣ 303 ጫማ ፣ 50 ካርቶን ሣሙና ፣ 3000 የትምህርት መገልገያዎች ፣ 389 ጆግ ፣ 502 የመኪና ጎማ ከመነዳሪያ ፣ 404 ሺህ ጆንያ ፣ 300 ሜትር ገመድ እና የተለያየ መጠን ያላቸው ኘላስቲክ ሸቶች በአብዛኛው ለተጎጂዎች መከፋፈሉ ታውቋል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ተጎጂዎችን መልሶ ለማቋቋም የሚለገሰው ዕርዳታ ተጠናክሮ የቀጠለ ሲሆን ፣ እስከ መስከረም 26 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ የመንግሥትና የግል ተቋማት ፣ ድርጅቶች ፣ ማህበራትና ግለሰቦች ፣ የአፍሪካ ህብረት ፣ የቻይና ፣ የጃጠንና ኦስትሪያ ቀይ መስቀል ማህበራት ፣ የውጭ መንግሥታት ፣ በውጭ አገር የኢትዮጵያ ኤምባሲ ሚስዮኖች ፣ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጳያውን ብር 38 ሚሊየን 409 ሺህ 363 ከ30 ሣንቲም በዓይነትና በገንዘብ በአመዝኤና በድሬዳዋ አስተዳደር ካውንስል በኩል ለግሰዋል፡፡

ከዚሁ ውስጥ በአመዝኤ በኩል 21 ሚሊየን 995 ሺህ 405 ከ88 ሳንቲም ፣ በድሬዳዋ አስተዳደር ካውንስል በኩል ደግሞ 5 ሚሊየን 800 ሺህ በጥሬ ገንዘብ መለገሱ ታውቋል፡፡


በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ
ስልክ. 5529259
ጠ.ሳ.ቁ 5686
ድረገጽ፣www.dppc.gov.et



ዜና አመዝኤ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲና ተባባሪዎቹ የሚያካሂዷቸውን የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት እንቅስቃሴዋችንና ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራትን የሚዘግብ ወርሃዊ ልሳን ነው

ቀሪው ግምቱ 10 ሚሊየን 613 ሺህ 957 ከ42 ሳንቲም በዓይነት የተገኘ ዕርዳታ ሲሆን ፣ ከዚሁ ውስጥ 6 ሚሊየን 13 ሺህ 957 ከ42 ሳንቲም በአመዝኤ ፣ 4 ሚሊየን 600 ሺህ ደግሞ በድሬዳዋ አስተዳደር ካውንስል በኩል የተለገሰ ነው::

## ለመስከረም ወር ከ 156 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታና ከ3,900 በላይ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች ተመድቧል፤

በተለያዩ ክልሎች በልዩ ልዩ የምግብ እጥረት መንስኤዎች ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው እና በጎርፍ አደጋ ለተፈናቀሉ ወገኖች ለመስከረም ወር የሚያስፈልጋቸው በጠቅላላው 156 ሺህ 388 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ተመድቧል:: ከዚህ የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 130 ሺህ 290 ኩንታል በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ፣ ቀሪው 26 ሺህ 098 ኩንታል ደግሞ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተመደበ መሆኑም ታውቋል:: ለመስከረም ወር ከተመደበው ጠቅላላ 156 ሺህ 388 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 141 ሺህ 691 ኩንታል ለመደበኛ ተረጂዎች ፣ ቀሪው 14 ሺህ 697 ኩንታል ደግሞ በጎርፍ አደጋ ለተፈናቀሉት ወገኖች የተመደበ መሆኑንም ለመረዳት ተችሏል::

ለየክልሎች የሚደረገው የዕርዳታ ድልድልም በየክልሉ እንደሚገኘው ችግር ስፋትና ጥልቀት የሚለያይ ነው:: በዚሁ መሠረት ለመስከረም ወር መደበኛ ተረጂዎች ከተመደበው ጠቅላላ 141 ሺህ 691 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ውስጥ ለኦሮሚያ 84 ሺህ 979 ኩንታል ፣ ለአማራ 27 ሺህ 729 ኩንታል ፣ ለሱማሌ 19 ሺህ 800 ኩንታል፣ ለደቡብ ህዝቦች 6 ሺህ 928 ኩንታል፣ ለአፋር 1ሺህ 927 ኩንታል እና ለትግራይ 328 ኩንታል ተመድቧል::

በተመሳሳይ ሁኔታም በተለያዩ ክልሎች በጎርፍ አደጋ ለተፈናቀሉ ወገኖች ከተመደበው ጠቅላላ 14 ሺህ 697 ኩንታል ውስጥ ለሱማሌ 7 ሺህ 450 ኩንታል ፣ ለአማራ 4 ሺህ 546 ኩንታል፣ ለድሬዳዋ 1 ሺህ 853 ኩንታል ፣ ለኦሮሚያ 389 ኩንታል እና ለደቡብ ህዝቦች 259 ኩንታል የተመደበ መሆኑ ታውቋል::

በተለያዩ ክልሎች በልዩ ልዩ የምግብ እጥረት መንስኤዎች ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው እና በጎርፍ አደጋ ለተፈናቀሉ ወገኖች ለመስከረም ወር የሚያስፈልጋቸው በጠቅላላው 156 ሺህ 388 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ተመድቧል::



ከዚህም በተጨማሪ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል በደቡብ ኦሞ ዞን ለሚገኙ የጎርፍ አደጋ ተፈናቃዮች ቀደም ሲል ከተላኩት ቁሳቁሶች በተጨማሪ በመስከረም ወር 1 ሺህ 519 ኩባያ ፣ 1 ሺህ 519 ኘላስቲክ ሳህን ፣ 217 ጀሪካን ፣ 217 ጆግ ፣ 434 ብርድልብሶች ፣ በድምሩ 3906 ልዩ ልዩ ቁሳቁሶች እና ለመጠለያ የሚሆኑ መጠናቸው 4✕50 የሆነ 5 ጥቅል ኘላስቲክ ሽቶች የተላኩ መሆኑን ከኤጀንሲው የዕርዳታ ኘሮግራሞች አፈጻጸም ክትትል መምሪያ የተገኘው መረጃ ያመለክታል::

# ብሔራዊ ዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴ ዕርዳታ ለማሰባሰብ በተዘጋጀ ረቂቅ ዕቅድ ላይ ተወያየ

● የተቋቋሙት ኮሚቴዎች ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለመግባት በዝግጅት ላይ ናቸው

በብሔራዊ የዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴው ሥር የተቋቋሙት ልዩ ልዩ ንዑስ ኮሚቴዎችም ዝርዝር የሥራ ዕቅዳቸውን ነድፈው እንቅስቀሴ ለመጀመር በዝግጅት ላይ መሆናቸው ተገለጠ::

ብሔራዊ ዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴው መስከረም 11 ቀን 1999 ዓ.ም ባደረገው የመጀመሪያ ስብሠባው ባሳለፍነው ክረምት በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በተከሰተው የጎርፍ አደጋ ሳቢያ ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉትን ዜጎች ለዘለቄታው ለማቋቋም የሚያስፈልገውን ገንዘብ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ለማሰባሰብ ያስችላል ተብሎ በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ተዘጋጅቶ በቀረበው ረቂቅ ዕቅድ ላይ ተወያይቷል:: በብሔራዊ የዕርዳታ



አሰባሳቢ ኮሚቴው ሥር የተቋቋሙት ልዩ ልዩ ንዑስ ኮሚቴዎችም ዝርዝር የሥራ ዕቅዳቸውን ነድፈው እንቅስቀሴ ለመጀመር በዝግጅት ላይ መሆናቸው ተገለጠ::

በዚሁ የኮሚቴው ስብሠባ ላይ እንደተጠ ቀሰውና በቀረበው ረቂቅ ዕቅድ ላይ እንደተመለከተው የጎርፍ አደጋ ተጎጅዎቹን ለዘለቄታው መልሶ ለማቋቋም የሚያስፈልገውን ገንዘብ ለማሰባሰብ በተጀመረው ጥረት ከሀገር ውስጥ መንግስታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፣ ከሀይማኖት ተቋማት ፣ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ፣ ከማህበራትና ከግለሠቦች እስካሁን የተገኘው ምላሽ በእጅጉ የሚያበረታታ ነው:: ይሁን እንጂ ይኸን ጉዳይ ለማስፈፀም ያስፈልጋል ተብሎ የታሰበው ገንዘብ ከፍተኛ እንደመሆኑ መጠን ዕርዳታውን ከሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ከሚገኙ ኢትዮጵያዊያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች የማሰባሰቡ ሥራ ተጠናክሮና በስፋት መቀጠ ል ይኖርበታል::

በዚሁ መሠረት ዕርዳታ የማሰባሰቡን ሥራ በስፋት ለመተግበር እና በሁሉም ደረጃ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለማሳተፍ አስፈላጊ የሆኑና መዋቀር የሚገባቸው ኮሚቴዎች በረቂቅ ዕቅዱ ቀርበው ሰፊ ውይይት ተደርጎባቸዋል::

በሠነዱ ላይ እንደተመለከተው ዕርዳታ የማሰባሰቡን ሥራ በስፋት ለማካሔድ የሚያስፈልጉ ኮሚቴዎች የቴሌቶን ኮሚቴ፣ የስፖርት ሙዚቃ ፊልምና ቴያትር ኮሚቴ፣ የእራት ምሽት ኮሚቴ ፣ የሎተሪ ኮሚቴ፣ የሀይማኖት ተቋማት ኮሚቴ ፣ የኢንፎርሜሽን ሥርጭትና ኘሮሞሽን ኮሚቴ ናቸው:: የእያንዳንዱ ኮሚቴ ተግባርና ሀላፊነትም በረቂቅ ዕቅዱ የተመለከተ ከመሆኑም በተጨማሪ የማዳበሪያ ውይይት ተደርጎበታል:: እያንዳንዱ ኮሚቴ ተግባርና ሀላፊነቱን ለመወጣት የሚያስችለውን የራሱን መርሀ ግብር እንደሚያዘጋጅና ይኸንኑ ተግባራዊ ካደረገ በኋላ በመጨረሻ ውጤቱን ለብሔራዊ ኮሚቴው እንደሚያቀርብም ተመልክቷል:: በየኮሚቴዎቹ ውስጥ

እያንዳንዱ ኮሚቴ በሚሠራበት መስክ መሠረት የሚመለከታቸው የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሥራ ሀላፊዎች እንዲሁም የሀይማኖት ተቋማት ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡

እነዚህ ኮሚቴዎች የጎርፍ ተጎጂዎችን ለዘለቄታው ለማቋቋም የሚያስፈልገውን ገንዘብ ለማሰባሰብ ሳይዘገዩ ወደተግባር መግባትና መንቀሳቀስ እንደሚገባቸው በውይይቱ ላይ የተጠቀሰ ከመሆኑም በላይ የኮሚቴው ሥራ በማዕከል ብቻ የተገደበ ሳይሆን ክልሎችንም በሠፊው የሚያሳትፍ መሆን እንደሚገባው ታምኖበታል፡፡

ከዚህም ሌላ በዚህ መልኩ ዕርዳታ ከሀገር ውስጥና ከውጭ የማሰባሰብና በአደጋ ጊዜ ለሚደርሱ ጉዳቶች አስቸኳይ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል አቅም የማጎልበቱ ሥራ አደጋ በደረሰ ጊዜ ብቻ የሚሠራ ሳይሆን በቋሚነት መከናወን የሚገባው በመሆኑ ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመነጋገር ቀጣይነት ኖሮት በቋሚነት የሚሠራበትን ሁኔታ ማመቻቸት አስፈላጊ እንደሆነ በኮሚቴው ውይይት ላይ የተነሳ ጉዳይ ነው፡፡

የኮሚቴ አባላቱ በረቂቅ ዕቅዱ ላይ ሠፊ ውይይት ካደረጉ በኋላ በስብሰባው ላይ የተሰጡት የማዳበሪያ አስተያየቶች ታክለውበት የመጨረሻ መልኩን እንዲይዝና ዕቅዱን ተግባራዊ የማድረጉ እንቅስቃሴ በቶሎ እንዲጀምር ተስማምተዋል፡፡

## ወላጆቻቸውን በጎርፍ አደጋ ያጡ ህፃናት ወደ ማሳደጊያ ተቋም እንዲገቡ ተደረገ

በድሬዳዋ ከተማ በደረሰው የጎርፍ አደጋ ሳቢያ ወላጆቻቸውን ያጡና ሰብሳቢና አሳዳጊ የሌላቸው ዕድሜአቸው ከ4 እስከ 13 ዓመት የሆኑ ስድስት ህፃናት በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ አማካይነት በቀጣዩ ህይወታቸው የሚያስፈልጋቸውን ተገቢ እንክብካቢና የትምህርት ድጋፍ ሊያገኙ ወደ ሚችሉት የወ/ሮ አበበች ጎበና ህፃናት ማሳደጊያና ልማት ድርጅት እንዲገቡ ተደርገዋል፡፡

በድሬዳዋ ከተማ በደረሰው የጎርፍ አደጋ ሳቢያ ወላጆቻቸውን ያጡና ሰብሳቢና አሳዳጊ የሌላቸው ዕድሜአቸው ከ4 እስከ 13 ዓመት የሆኑ ስድስት ህፃናት በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ አማካይነት በቀጣዩ ህይወታቸው የሚያስፈልጋቸውን ተገቢ እንክብካቢና የትምህርት ድጋፍ ሊያገኙ ወደ ሚችሉት የወ/ሮ አበበች ጎበና ህፃናት ማሳደጊያና ልማት ድርጅት እንዲገቡ ተደርገዋል፡፡



ኤጀንሲው ህፃናቱን መስከረም 8 ቀን 1999 ዓ.ም በተደረገ የርክክብ ሥነስርዓት የማሳደጊያው ድርጅት መሥራችና ዳይሬክተር ለሆኑት ወ/ሮ አበበች ጎበና አስረክቧል፡፡

በዚሁ የርክክብ ሥነሥርዓት ላይ ወ/ሮ አበበች ጎበና ባደረጉት ንግግር የጎርፍ አደጋ በሀገሩ የተለያዩ አካባቢዎች ለበርካ ዜጎች ህይወት መጥፋት፣ የንብረት መውደምና በብዙ ሺህ ለሚቆጠኝ ዜጎች ከቤት ንብረቸው መፈናቀል ምክንያት መሆኑንና ይኸ እጅግ የሚያሳዝንና ተጎጂዎቹን ለመደግ የሁሉንም ርብርብ ይጠ

ይኝል ብለዋል:: አያይዘውም ከምንም በላይ ደግሞ የህፃናት በዚህ መልኩ ወላጆቻቸውን ማጣትና ያለ ሰብሳቢና አሳዳጊ መቅረት ስኝትን የሚነካ ነው ያሉት ወ/ሮ አበበች ተጎጂ ወገኖቻችንን በምንችለው ሁሉ ለመደገፍ በገባነው ቃል መሠረት እነዚህን በአደጋው ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናት ዛሬ ተረክበን እያንዳንዳቸው የ18 ዓመት እስኪሞላቸው ድረስ ለኑሮአቸውና ለትምህርቸው አስፈላጊውን ድጋፍ እናደርግላቸዋለን ሲሉ አረጋግጠ ዋል::

ከዚያም በኃላ ልጆቹ ትምህርቸውን ሲጨርሱ በድርጅቱ መርህ ግብር መሠረት በተለያዩ የሥራ መስኮች ተሠማርተው እራሳቸውን እንዲረዱ የልዩ ሥልጠናና የማቋቋሚያ ድጋፍ እንደሚደረግላቸው ገልፀዋል:: በማከልም ወ/ሮ አበበች ጎበና ህፃናቱ በማሳደጊያና መንከባከቢያ ድርጅቱ በሚቆዩበት ጊዜ ለእየንዳንዳቸው በዓመት ብር 5 ሺህ ወጭ እንደሚደረግ በመግለጽ ወደፊትም በዚህ አይነት በአደጋ ወላጆቻቸውን የሚያጡ ህፃናትን ተቀብለው ወደ ድርጅቸው ለማስገባት እና አስፈላጊውን ድጋፍ ለመስጠት ዝግጁ መሆናቸውን አመልክተዋል::

በጎርፍ አደጋ ወላጆቻቸውን ያጡትን ህፃናት ለወ/ሮ አበበች ጎበና ያስረከቡት የአመዝኤ ዋና ዳይሬክተር ሲሞን መቻለ በበኩላቸው ወላጆቻቸውን በአደጋ ሳቢያ አጥተው ያለሰብሳቢና አሳዳጊ ለሚቀሩ ህፃናት አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ የመንግስትና የሕዝብ ኃላፊነት እንደመሆኑ መጠን በዚህ ረገድ ወ/ሮ አበበች ከዚህ ቀደምም ሆነ አሁን እያደረጉት የለው ድጋፍ በአርአያነት የሚጠ ቀስ ነው ካሉ በኃላ ድርጅቱ ምንም እንኳን ወላጅ እናትና አባትን የሚተካ ባይሆንም ለልጆቹ ኑሮና ትምህርት አስፈላጊውን ሁሉ በማድረግ አድገው ለቁም ነገር የሚበቁ ዜጐች እንደሚያደርጋቸው ሙሉ እምነቴ ነው ብለዋል:: በማከልም አቶ ሲሞን ህፃናቱ ወ/ሮ አበበችን እንደ እናቸው ድርጅቱን ደግሞ እንደራሳቸው ቤት በማድረግ በርትተው እንዲማሩና ለቁም ነገር እንዲበቁ መልዕክታቸውን አስተላልፈውላቸዋል::

## የአመዝኤ የ1998 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም አጥጋቢ እንደነበር ተገለፀ::

የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ እና የተጠሪ መሥሪያ ቤቶች የ1998 ዓ.ም በጀት ዓመት የ4ኛ ሩብ ዓመትና ዓመታዊ የፊዝካል ሥራዎች ዕቅድ አፈጻጸምና የበጀት አጠቃቀም በአጠቃላይ መልኩ በአጥጋቢ ሁኔታ መከናወኑ ተገለፀ::

መስከረም 12 ቀን 1998 ዓ.ም በፖሊሲ፣ ኘላንና ኘሮግራም መምሪያ አማካይነት ለኤጀንሲው የሥራ ኃላፊዎች ለውይይት በቀረበው ሰነድ ላይ እንደተመለከተው ያለፈው የበጀት ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ አበረታች ነው::



> የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ እና የተጠሪ መሥሪያ ቤቶች የ1998 ዓ.ም በጀት ዓመት የ4ኛ ሩብ ዓመትና ዓመታዊ የፊዝካል ሥራዎች ዕቅድ አፈጻጸምና የበጀት አጠቃቀም በአጠቃላይ መልኩ በአጥጋቢ ሁኔታ መከናወኑ ተገለፀ።

በተለይም የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ኘሮግራሙ አካላት ከሆኑት መካከል በ1997 ዓ.ም ተጀምረው ያልተጠናቀቁና አዳዲስ የ«ኩዊክ ዊንስ» ሥራዎችን ማጠናቀቅ ፣ በ12 መምሪያዎችና አገልግሎቶች በ2 ተጠሪ መሥሪያ ቤቶች በማዕከላዊ መጋዘኖች ላይ የተጀመሩ የአሠራርና የአገልግሎት ማሻሻያ ጥናቶች አጥርቶና አጠናቅሮ ማጠናቀቅ፣ የክትትልና ግምገማ መመሪያውን ተከትሎ ግምገማ ማካሄድ ፣ የመሥሪያ ቤቱንና የተጠሪ መሥሪያ ቤቶችን ራዕይ ተልዕኮና እሴቶች ቃቃቶ ማስተካከል፣ በተለያዩ ደረጃ ለሚገኙ 60 የኤጀንሲው ሠራተኞች የኮምፒዩተር ሥልጠና መስጠት ፣ 30 ኮምፒዩተሮችን ለሚያስፈልጋቸው የሥራ ዘርፎች ማቅረብና ድጋፍ መስጠት ፣ የተቀላጠፈ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎት መስጠትና የ1996/97 ዕቅድን መገምገም ከታቀደው መቶ በመቶና ከዚያም በላይ እንደተከናወኑ ከማጠቃለያ ሪፖርቱና ከተደረገው ውይይት ለመረዳት ተችሏል።

በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሥራዎችም የ1997 ዓ.ም የበልግ ፣ የአርብቶ አደር አካባቢ የዋና የዝናብ ወቅት የምግብ አቅርቦትና ሪፖርት ፣ በሰብል አብቃይና አርብቶ አደር አካባቢዎች የ1998 ዓ.ም የተለያዩ የመኸር ፣ የበልግና የዝናብ ወቅቶች ጥናቶችን ማካሄድና ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ማሰራጨት ከታቀደው መቶ በመቶ ተከናውነዋል። በተጨማሪም በዩኒሴፍ ድጋፍ የሚከናወኑ ሥራዎችን መከታተልና በዕቅድ መሠረት ተግባራዊ እንዲሆኑ በማድረግ ረገድ ተመሳሳይ የሆነ የዕቅድ አፈፃፀም መታየቱ ተጠቁሟል።

የዕርዳታ ሃብት የማሰባሰብ ሥራዎችን በተመለከተ ካንዳንድ ግቦች በስተቀር አብዛኛው በአጥጋቢ መልኩ መከናወናቸው ታውቋል። በተለይም ለኢመርጀንሲ ኑትሪሽን ኮኦርዲኔሽን ዩኒት ማቋቋሚያ ፣ ለአመዝኤ የመረጃ ማዕከልና ለመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር ማጠናከሪያ ከዕቅድ በላይ ከፍተኛ መጠን ያለው የዕርዳታ ሀብት ለማሰባሰብ መቻሉን ለውይይት የቀረበው የማጠቃለያ ሪፖርት ያሳያል።

በዕርዳታ ኘሮግራሞች የሥራ ዘርፍ በዕቅድ ተይዘው ከተከናወኑት አበይት ተግባራት መካከል የአስቸኳይ /ኢመርጀንሲ/ ሁኔታዎች በተከሰተባቸው አካባቢዎች የሰብዓዊ ዕርዳታ አቅርቦት ሥራዎችን በማተባበር የተከሰቱትን አደጋዎች ለማቋቋም ጥረት መደረጉ ተጠቅሷል።

ከዚህም በተጨማሪ በሎጂስቲክስ ትራንስፖርት ፣ በመጠባበቂያ ምግብ ክምችት፣ በአመዝ ፈንድ አስተዳደር ፣ በሴቶች ጉዳይ ፣ በፋይናንስ ፣ በኦዲትና ኢንስፔክሽን ፣ በሽያጭ ጨረታ ፣ በግዥ ጨረታ ፣ በፖሊሲ ኘላንና ኘሮግራም ፣ በማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ፣ በአስተዳደር አገልግሎት ፣ ፣ በሕግ አገልግሎት ሥራዎች ረገድ የነበረው አፈፃፀም በተመለከተ በቀረበው ሪፖርት ላይ ተመስርቶ ውይይት ተደርጓል።

በዕቅድ ተይዘው ሳይከናወኑ የቀሩትን የአመዝ ፖሊሲን ማሻሻል ፣ የውጤት ተኮር አሠራር መዘርጋት ፣ የአደረጃጀትና የሥራ መደቦች ማሻሻያ ማድረግ ፣ የአመዝ ፈንድ አቅም ማጐልበት ፣ ኢንትራኔት መዘርጋት ፣ የመያድ ዓመታዊ ዕቅድ ማጠናከርና ሌሎችም ተግባራት በቀጣዩ ዓመት ዕቅድ ውስጥ ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸው ለተግባራዊነታቸው ያላሰለሰ ጥረት ሊደረግ እንደሚገባ ማሳሰቢያ ተሰጥቷል።

በዕለቱ በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ የ1999 ዓ.ም በጀት ዓመት ዕቅድ መርሐ ግብር ላይም ውይይት የተደረገ ሲሆን በሚከናወኑት ዋና ዋና ተግባራት ላይ አስተያየቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች በተሳታፊዎቹ ቀርበዋል።

